# - 30 -

# የሴት ልጅ ክብር

## ሴትን ልጅ ማብቃት

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች የእስልምናን መልዕክት ለማድረስ ብለው ወደ አንድ ከተማ ሲገቡ ከመልዕክተኛው የተቀበሉትን መልዕክት ውብ በሆነ መልኩ ነው የሚያስተላልፉት። እንዲህ ይላል የርሣቸው መልዕክት:-"እኔ የመጣሁት ከባሮች ባርነት የባሮች ጌታ ወደሆነው ባርነት ነፃ ላወጣችሁ ነው።"

በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ አንድ ምርጥ የሆነ መልዕክት አለ። በቃላቱ ውስጥ የተደበቀ ሲሆን ሁሉንም በተለይ ተጎጂ የሆነውን የማኅበረሰብ ክፍል ለማብቃት እንዲሁም ወደ ነፃነት ለመድረስ ትክክለኛው ቁልፍ ነው።

ምን መሰለህ ...አንተ ወይም እኔ ከፈጣሪያችን ውጭ አንድ ነገር እንዲገዛን ከፈቀድን፤ስኬታችንን፣ ውድቀታችንን፣ ደስታችንን፣ ጥቅማችንን፣ ከዚያ ነገር አያይዘን በዝምታ ነገሮችን የምንቀበል ከሆነ ያ ጎጂ የሆነ ባርነት ነው። ያ ራሴን የስኬቴ እና የውድቀቴ ሁሉ ፈላጭ ቆራጭ ወሳኝ አድርጎ የሚያቀርበው ነገር እኔን የሚቆጣጠር አለቃዬ ነው የሚሆነው ማለት ነው።

ሴትን ልጅ ሊገዛ የሚችልና አለቃዋ የሆነ ነገር በየጊዜው የተለያየ መልክ፣ ይዞ ዘመናትን ተሻግሮ ዛሬ እዚህ ላይ ደርሷል። ለረጅም ዘመን ለሴት ልጅ መለኪያ ተደርጎ በስፋት የሚታወቀው ግን ወንድ ነው። ግና ብዙን ጊዜ እኛ የምንረሳው ነገር ቢኖር አላህ ለሴት ልጅ ክብር የሠጠው ከሱ (ሱ.ወ.) አንፃር ባላት ግንኙነት እንጂ ከወንድ ልጅ ጋር ባላት አቀራረብ አይደለም። ግና ምዕራባውያን የሴትነት ነፃነት አቀንቃኞች አምላክን ከሥፍራው በማንሳታቸው እንደ መለኪያ የቀረው ወንድ ልጅ ብቻ ነው። ስለሆነም ምዕራባውያን የሴትነት ነፃነት አቀንቃኞች ወንድ ልጅን መለኪያቸው ለማድረግ ተገደዱ። ይህን በማድረጋቸውም ምክንያት ለሴት ልጅ የተሳሳተ መለኪያ ለመቀበል ቻሉ። ሴት ልጅ "ሙሉ ሰው" የምትሆነው እንደ መለኪያዋ እንደ ወንድ ልጅ ስትሆን ብቻ ነው አሉ።

ወንድ ልጅ ፀጉሩን አጭር አድርጎ ሲቆረጥ ሴቷም ካልተቆረጥኩ አለች። ወንድ ልጅ ከጦር ሠራዊቱ ጋር ሲቀላቀል ሴቷም እኔም መሳተፍ ይገባኛል አለች። እነኚህን ነገሮች ያሰበችው ወድዳና ከመጀመርያው አስባበት ሳይሆን "መለኪያ/ውሃ ልክ" ነው ተብሎ የታሰበው ወንድ ልጅ ስለተሳተፈበት ብቻ ነው።



CamScanner
CamScanner

እሷ ያላስተዋለችው ነገር ቢኖር አላህ (ሱ.ወ.) ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን በተመሳሳይነታቸው ሳይሆን በልዩነታቸው ለሁለቱም ክብር የሠጠ መሆኑን ነው። ግና ወንዶችን እንደ ሰውነት ውሃ ልክ የተቀበልናቸው እንደሆነ የሴት ብቻ የሆነ ነገር ሁሉ ዝቅ ብሎ አሊያም ምንም ሆኖ ይታየናል። የስስ ስሜት (እዝነት) ባለቤት መሆንና የተሟላ የእናትነት ባህሪን መላበስ ድክመትና ልፍስፍስነት ይመስለናል። የወንድ ነው ተብሎ በሚታሰበው በአካላዊ ሻካራነት እና የሴት ነው ተብሎ በሚታወቀው ከፍ ያለ ርህራሄ መካከል በሚደረገው ጦርነት ወንዳወንድነት ተመራጭና የበላይ ሆኖ መታየቱ ይገርማል።

ወንድ ልጅ ያለው ነገር ሁሉ ጥሩ ነው ብለን የምናስብ ከሆነ የራሣችንን ሚና እንዘነጋለን።በሁሉ ነገርውስጥ ከወንድ ልጅ አንፃር ምላሽ ምንሰጥ ነው የሚሆነው። ወንድ ልጅ የሆነ ነገር ካለው እኛም እንዲኖረን እንፈልጋለን። ወንድ ልጅ የመጀመርያው የሶላት ሰፍ ላይ የሚሰግድ ከሆነ ያ ቦታ ለኛም ምርጥ ሆኖ ይታየናል። ስለሆነም በመጀመርያው ሰልፍ ላይ ለመስገድ እንመኛለን። ወንድ ልጅ ኢማም ከሆነ፤ ኢማም የሆነ ሰው ለአላህ የቀረበ እንደሆነ ይሰማናል፤ እናም ሶላት ካልመራን፣ ካላሰገድን እንላለን። በአንድ የሆነ ቦታ ላይ የተሳሳተ ግንዛቤ በመያዛችን በዚህች ምድር ላይ የመምራት ዕድል መሠጠት አንድ ሰው አላህ ዘንድ ያለው ደረጃ ከፍ ያለ ነው ብለን እናስባለን።

ሙስሊሟ ሴት በዚህ መልኩ ራሷን ዝቅ ማድረግና መጉዳት የለባትም። ውሃ ልኳ አምላኳ ነው። ከሱ አንፃር ነው ራሷን መመዘንና መገምገም ያለባት። አምላኳ ነው ደረጃዋን የሚያስቀምጥላት፣ ክብሯን የሚመዝንላት፣ የሚመዝናት ወንድ ልጅ አያስፈልጋትም። ከወንድ ልጅ አንፃርም ራሷን መመዘን የለባትም።

ግልጹን ለመናገር እኛ ሴቶች ክብራችንን የምናወርደው ያልሆንነውን ነገር ለመሆን ስንሞክር ነው። በርግጥም ወንድ መሆን አንፈልግም። እኛ ሴቶች በርግጥ እውነተኛ ነፃነት ላይ ልንደርስ የምንችለው ወንዶችን መምሰል ስናቆምና በአምላካችን የተሠጠንን ውበትና ልዩነታችንን ስናከብር እና ዋጋ ስንሠጠው ብቻ ነው።

ሌላው በስፋት የተሠራጨውና ለሴት ልጅ እንደ አለቃና መሪ ሆኖ የተቀመጠው የማንነቷ መለኪያ "ውበት" የሚለው ነው። ከልጅነታችን ጀምሮ እኛ ሴቶች በማኅበረሰባችን የተሠጠን ግልጽ የሆነ ትምህርት አለ። "ቀጭን ሁኚ"፣ "አማላይ ሁኚ"፣ "ሳቢ ሁኚ" ... ካልሆነ ምንም ዋጋ የለሽም የሚል መልዕክት።

ስለሆነም ለዚሁ ስንል ሜክ አፕ መቀባት፣ ቁምጣ እና ሚኒ መልበስ እንዳለብን ተነገረን። ሕይወታችንን፣ ሰውነታችንና ክብራችንን ቆንጆ ሆኖ ለመታየት ስንል አሳልፈን መስጠት እንዳለብን ታዘዝን። የቱን ያህል ብንሠራና ብናደርግም ክብር የሚኖረን ወንዶችን በምናስደስተውና ለነርሱ ቆንጆ ሆነን በምንታየው ልክ መሆኑን እስከማመን ደረስን።



CamScanner

CamScanner

ስለሆነም ነው ፊታችንን ለመዋቢያ ዕቃዎች እንዲሁም ሰውነታችንን ለማስታወቂያ ለመሸጥ ያቀረብነው።

ያኔ በርግጥ ባሮች ነበርን። ግና ነፃነት እንዳለን አስተማሩን። የነርሱ ቁስና ዕቃ ነበርን፤ ግና እነርሱ ዕድገት ነው ብለው አማሉልን። በሕይወት ውስጥ የኛ ዓላማ ማሳያና ማሻሻጫ፣ እንዲሁም ወንድን ልጅ መሳብ እና ውብ መስሎ መታየት እንደሆነ ስላስተማሩን የኛ ገላ የተፈጠረው ለመኪናቸው ማሻሻጫ መሆኑን ማመን ግድ ነበር። ግና ይህን ሁሉ ሲሉ ውሸታቸውን ነበር።

ገላሽም ሆነ ነፍስሽ የተፈጠሩት ለሌላ ከፍ ላለ ነገር ነው። አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّا خَلَقۡنَٰكُم مِّن ذَكَرٖ وَأُنثَىٰ وَجَعَلۡنَٰكُمۡ شُعُوبٗا وَقَبَآئِلَ لِتَعَارَفُوٓاْۚ إِنَّ أَكۡرَمَكُمۡ عِندَ ٱللَّهِ أَتۡقَىٰكُمۡۚ ﴾

**«እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፤ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ። አላህ ዘንድ በላጪችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው።»** (አል-ሑጁራት ፡ 13)

ስለዚህ አንቺ ሴት ልጅ ሆይ የተከበርሽ ነሽ። ግና ከወንድ ልጅ ጋር ባለሽ ግንኙነት አንጻር ማለትም እነርሱን ከመሆን አሊያም እነርሱን ከማስደሰት አንፃር አይደለም ክብርሽ የሚለካው። እንደ ሴት ልጅ ያንቺ ክብር የሚለካው በወገብሽ ቁጥር ወይም በሚያደንቅሽ ወንድ ብዛት አይደለም። እንደ ሰው ልጅ ያንቺ ክብርና ደረጃ የሚለካው ከፍ ባለ መለኪያ ነው። በመልካምነት እና ለአላህ በሚኖር ፍራቻ ነው። በምድር ላይ ያንቺ የመፈጠር ዓላማ የፋሽን መጽሔቶች ከሚሉት ከፍ ያለ ነው። ማራኪ እና ለወንዶች ቀልብ ሳቢ ሆኖ መታየት አይደለም።

የኛ ምሉእነት የሚገኘው ከአምላካችን እና ከአምላካችን ጋር በሚኖረን ግንኙነት ነው። ግና አሁንም ከልጅነታችን ጀምሮ እኛ ሴቶች በወንድ ልጅ እስካልተሟላን ድረስ ሙሉ የሰውነት ደረጃ ፈጽሞ ልንደርስ እንደማንችል ነው የተነገረን። እንደ ሲንደሬላ ታሪክ ሁሉ ልዑሉ ወንድ መጥቶ እስካላዳነን ድረስ እኛ ረዳት የለሽ ደካሞች እንደሆንን ነው ማኅበረሰባችን ያስተማረን። እንደ ምርጥ እንቅልፍ ሁሉ ልዑሉ መጥቶ በስሱ ካልሳመን በስተቀር የኛ ሕይወት ሙሉ በሙሉ ሊጀምር እንደማይችል ነው የተነገረን። ማወቅ ያለብን ነገር የትኛውም ልዑል ሕይወታችንን ሊያሟላው አይችልም። የትኛውም ጀግና አያድነንም። የሚያድነን አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ ነው።

በርግጥ ያንቺ ልዑል የሰው ልጅ ሊሆን ይችላል። ያ ግን የሕይወት አጋርሽ እንጂ አዳኝሽ



CamScanner

CamScanner

ሊሆን አይችልም። እሱም የዐይን ማረፊያሽ እንጂ የሕይወትሽ ማቆያ ሳንባሽ አየር አይደለም። አየርሽ አምላክሽ ነው። መዳኛሽም እሱ ነው። ምሉዕነትሽ የሚረጋገጠውም ወደሱ ስትቀርቢ እንጂ እሱ ወደፈጠረው ነገር ስትቀርቢ አይደለም። ለልዑልም ሆነ ለፋሽን፣ ለውበትም ለስታይልም በመቅረብ አይደለም።

ስለሆነም እንድትነሺ እፈልጋለሁ። ተነስተሽ ለዓለም ሁሉ የማንም ባርያ እንዳልሆንሽ የፋሽን፣ የውበት፣ የወንድ፣ ባርያ እንዳልሆንሽ አስረግጠሽ መንገር ይኖርብሻል። ባርነትሽ ለአላህ እና ለአላህ ብቻ ነው። ወደዚህ ዓለም የመጣሽው አምላክሽን ለማስደሰት እንጂ በገላሽ ወንዶችን ለማስደሰት እንዳልሆነ ተነስተሽ ለዓለም ሁሉ እንድትናገሪ እጠይቅሻለሁ። ስለሆነም ነፃ እናወጣሻለን ብለው ለሚመኙ ሁሉ በራስ የመተማመን መንፈስ ፈገግ ብለሽ "እገዛ አያስፈልገኝም፤ አመሰግናለሁ።" ልትያቸው ይገባል።.

ወደዚህ ዓለም የመጣሽው በአደባባይ ለቅራቅንቦዎቻቸው ማሻሻጫና ለማሳያ እንዳልሆነ ንገርያቸው። ሰውነትሽም ለአደባባይ ገበያ የሚቀርብ እንዳልሆነ አሳውቂያቸው። ከሰውነት ደረጃ ወርደሽ የምትታዪ ቁስ እንዳልሆንሽ ዓለም ሁሉ ይወቅ። እግሮችሽም የጫማ መሸጫ መለኪያ አይደሉም። አንቺ ነፍስ ያለሽ ሰው ነሽ፣ አዕምሮ አለሽ፣ የአላህ ባርያና አገልጋይ ነሽ። ክብርሽ የሚለካው በነፍስሽ ውበት ነው፤ በልብሽ ጥራት እና በመልካም ሥነምግባርሽ ነው። ስለሆነም የነርሱ የውበት መለኪያ አምላኪ መሆን የለብሽም። የነርሱ ፋሽን ተከታይም አትሁኚ። መከተል እና እጅ መስጠት ያለብሽ ከፍ ላለ ነገር ይሁን።

ስለሆነም ሴት ልጅ የት እና እንዴት መብቃት ይችላሉ ለሚለው ምላሽ ለመስጠት ወደ አላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባ ንግግር መመለስ ያስፈልጋል። እውነተኛ ነጻነት እና መብቃት የሚረጋገጠው አንድን ሰው ከሌሎች ገዢዎች፣ ከሌሎች አለቃዎች እና ከሌሎች መለኪያዎች ነፃ በማውጣት ነው።

እንደ ሙስሊም ሴትነታችን ከዝምተኛው ባርነት ነጻ ወጥተናል። ክብራችንን በውበት እና በፋሽን የሚለካ ማኅበረሰብ አንፈልግም። ለመከበር እንደ ወንድ መሆን አያስፈልገንም። እንዲያድነን እና እንዲያሟላልን ብለን የምንጠብቀው ልዑል አያስፈልገንም። ጥቅማችን፣ ክብራችን፣ ደህንነታችን እና ምሉእነታችን በባሮች ላይ ጥገኛ አይደለም።

በባሮች ጌታ ላይ እንጂ።



CamScanner
CamScanner

# - 31 -

## መልዕክት ላሳደገኝ ማኅበረሰብ

ልጅ እያለሁ "Ugly Duckling/ አስቀያሚው ዳክዬ" በሚለው ተረት እየተነበበልኝ ነበር ያደግኩት። ለብዙ ዓመታት እሷ እኔ ነኝ ብዬ ተቀብዬ ኖርኩ። ማኅበረሰቤ ሆይ! ለረጅም ዘመናት የውሃ ልኮቹ (ወንዶች) መጥፎ ቅጂ እንጂ ሌላ ምንም እንዳልሆንኩ ነበር ያስተማርከኝ።

በምፈልገው መልኩ መሮጥ አልቻልኩም፤ ወይም ማንሳት የምችለውን ያህል ክብደት ለማንሳት ዕድል አልተሠጠኝም። ሁልጊዜ የማለቅስለትን ገንዘብ ማግኘት የነበረብኝን ያህል አላገኘሁም። ከማይመለከተኝ ጎራ በወንዶች በረት ውስጥ ነው ያደግኩት።

ግና ወንድ መሆን ሳልችል ስቀርና ወንድ እንዳማልሆን ሳውቅ፤ እሱን ማስደሰትን ብቻ ምርጫዬ አደረግኩኝ። የሱን መዋቢያ ተጠቀምኩ። የሱን ቁምጣ እና ሚኒ ለበስኩ። ሕይወቴን፣ ሰውነቴን፣ ክብሬን ለሱ ቆንጆ መስሎ ለመታየት ብዬ አሳልፌ ሰጠሁ። የቱን ያህል ባደርግም አለቃዬን ከማስደሰትና ለሱ ቆንጆ ሆኖ ከመታየት በላይ የሌለ ነገር እንደሌለ አውቃለሁ። ስለሆነም ነው ሕይወቴን በሙሉ ፊቴን ለመዋቢያ ዕቃዎች እና ሰውነቴን ላንተ እንደ ሸቀጥ ያቀረብኩት።

በርግጥ ባርያ ነበርኩ። ግና አንተ ነፃነት ነው ብለህ አስተማርከኝ። ያንተ ቁስ ነበርኩ፤ ግና አንተ ዕድገት ነው፣ መሠልጠን ነው ብለህ ማልከልኝ። በሕይወት ውስጥ የኔ ዓላማ ለማሻሻጫ፣ ለመሳቢያ እና ለወንድ ልጅ ውብ መስሎ መታየት መሆኑን አስተማርከኝ። የኔ ገላ የተፈጠረው ያንተን መኪና ለማሻሻጥ መሆኑን አሳመንከኝ። አስቀያሚዋ ዳክዬ መሆኔን እየነገርክ አሳደግከኝ። ግና ውሸትህን ነበር።

ግና ሃይማኖቴ ኢስላም ውቧ ዝዬ መሆኔን ነው የነገረኝ። እኔ ልዩ ነኝ። የተለየሁ እና ውብ። ሰውነቴም ሆነ ነፍሴ የተፈጠሩት ለሌላ ከፍ ላለ ነገር ነው። አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፦

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّا خَلَقۡنَٰكُم مِّن ذَكَرٖ وَأُنثَىٰ وَجَعَلۡنَٰكُمۡ شُعُوبٗا وَقَبَآئِلَ لِتَعَارَفُوٓاْۚ إِنَّ أَكۡرَمَكُمۡ عِندَ ٱللَّهِ أَتۡقَىٰكُمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٞ ﴾

**«እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፤ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፤ አላህ ዘንድ በላጫችሁ፣ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፤ አላህ ግልጽን በዋቂ ውስጥንም አዋቂ ነው።»** (አል-ሑጁራት ፡ 13)



CamScanner
CamScanner

ስለዚህ እኔ የተከበርኩኝ ነኝ። ከወንድ ልጅ ጋር ካለኝ ግንኙነት አንጻር አይደለም ክብሬ የሚለካውም ሆነ እኔነቴ የሚመዘነው። እንደ ሴት ልጅ የኔ ክብር የሚለካው በወገቤ ቁጥር ወይም በሚያደንቀኝ ወንድ ብዛት አይደለም። እንደ ሰው ልጅ የኔ ማንነትና ደረጃ የሚለካው ከፍ ባለ መለኪያ ነው። በመልካምነት እና ለአላህ ባለኝ ፍራቻ ነው የሚለካው። በምድር ላይ የኔ የመፈጠር ዓላማ የፋሽን መጽሔቶች ከሚሉት ከፍ ያለ ነው። ማራኪ እና ለወንዶች ቀልብ ሳቢ ሆኖ መታየት አይደለም።

እንዲሁም አምላኬ እንድሸፈን መክሮኛል። ውበቴን እንድደብቅ አዞኛል። እዚህ ምድር ላይ የመጣሁት በሰውነቴ ማራኪነት ወንዶችን ለማማለልና ለማስደሰት አይደለም። አምላኬን ለማስደሰት ነው የመጣሁት። አላህ ሴቶችን ያከበረው የሴት ልጅ ሰውነት መከበር እና መሸፈን እንዳለበት በማዘዝ ነው። መታየት ያለበት ለሚገባው ሰው ብቻ ነው። ለሚያገባት ወንድ።

ስለሆነም "ነጻ ሊያወጡኝ" ለሚመኙ ወገኖች ሁሉ ማለት የምችለው አንድ ነገር ብቻ ነው - "አመሰግናለሁ፣ አመሰግናለሁ።" ... "እገዛችሁን አልሻም አመሰግናለሁ።"

እዚህ የመጣሁት በአደባባይ ለማሻሻጫነት አይደለም። ሰውነቴም ለአደባባይ የሚቀርብ ሸቀጥ አይደለም። ከሰውነት ደረጃ ወርጄ እንደ ቁስ መታየት የለብኝም።የጫማ የመሸጫ እግሮች አይደለሁም። እኔ ሕይወት ያለኝ ፍጡር ነኝ። እኔ ነፍስ ነኝ፣ እኔ አዕምሮ አለኝ፣ ባርነቴም አገልጋይነቴም ለፈጠረኝ ጌታ ለአላህ (ሱ.ወ.) ብቻ ነው። እኔ የምገለጸው በነፍሴ ውበት እንጂ በሌላ አይደለም፤ በልቤ ጥራት እና በመልካም ሥነምግባር ነው የምመዘነው። ስለሆነም ያንተ የውበት መለኪያ አምላኪ አይደለሁም። ላንተ የፋሽን አስተምህሮም እጅ የምሰጥ፣ የምማልል የምከተል አይደለሁም። እኔ የምከተለው እና እጅ የምሠጠው ከፍ ላለ ነገር ነው።

ውበቴን በአደባባይ ከማስጣት ይልቅ በሒጃቤ በመሸፈን እምነቴን እገልፃለሁ። እንደ ሰው ልጅ የኔ ዋጋ የሚለካው ከአምላኬ ጋር ባለኝ ግንኙነት እንጂ በአደባባይ ባሠጣሁት ይህም ያም በሚያየው ውበቴ አይደለም። አንተን ሊስብ የሚችለውን የሰውነት ክፍሌን አሸፍናለሁ። ማየት ብትፈልግ እንኳን አታየኝም። አካሌን አታይም።ገላዬ ይናፍቅሃል አታየኝም። እኔን ማየት ያለብህ በማንነቴ ብቻ ነው። እኔ የፈጣሪዬ አገልጋይ ነኝ።

ምን መሰለህ .. እንደ ሙስሊም ሴትነቴ ከዝምተኛው ባርነት ነጻ ወጥቻለሁ። ምላሼ በምድር ላይ ላሉ የፈጣሪ ባሮች አይደለም። ንጉሣቸው ለሆነው ጌታ እንጂ።



CamScanner
CamScanner